# የደም ንግድ

ባለፉት አመታት በአገራችን የተካሄደዉን እልህ አስጨራሽና ዛሪም ለዉጤት ያልበቃዉን ህዝባዊ ትግል መሰረታዊ ጠንቅ ለማወቅ አያሌ የፖለቲካ ሰወች ደፋ ቀና ሲሉ ቆይተዋል

ፖለቲካ ድርጅቶች መጭዉ ዘመን ብሩህ ተስፋ ሊኖረዉ እንደሚችል በማስተማር በማደራጀት እና ለለዉጥ እንዲዘጋጅ በማድረግ ያስጨበጡት ዉጤት ህያዉ ታሪካቸዉ ነዉ

የህሊናዊና ነባራዊ ሁኔታ ኋላ ቀርነት በዋናነት መነሻ ይሁን እንጅ ይህን ሁሉ ገብ ኋላ ቀርነት ለመለጥ የተነሱ ፖለቲካ ድርጅቶች ሆኑ ግለሰቦች የችግሩ አቀጣጣይ ከመሆን ያለፈ ዘላቂ መፍትሄ ሊያገኙ አልቻሉም

አዲስ የሚፈጠሩ ፖለቲካ ድርጅቶችም የትግል አላማቸወ ያለፈዉን በማዉገዝና በመኮነን ላይ ብቻ ያተኮረ በመሆኑ ያላንዳች ለዉጥ ሁሉም ተያይዘዉ ባለህበት እርገጥ ሲሉ እያየናቸዉ ነዉ

የሚገርመዉ አመታት በሙሉ የሚነሱ የፖለቲካ ቃላቶች እና የትግል ስልቶች ያልተቀየሩበት ድርጅት አለ የዘመኑ ፖለቲካ ተቀይሯል ከኋላችን የተፈጠሩና ስለ ነፃነት ስለ አንድነት ስለሰላም ስለእድገት ስለ ዲሞክራሲያዊ ህዝባዊመንግስት ምስረታ ስለ ትጥቅ ትግል ያስተማርናቸዉ አገሮች አንድ ሆነዉ በአንድነት ለመጮኽ በሙብቃታቸዉ ዛሬ ከራሳቸዉ አልፈዉ እንደኛ ላሉ አገሮች ጥብቅና መቆም ከጀመሩ ሠንበትበት አሉ

የኛ ፖለቲከኞች በተበጣጠሰና በተናጠል የሚደረጉ ጥረቶች ደካማ ሰለመሆናቸዉ እንዳላስተማሩና ቡዙ ላለመራመድ የሚገደዱበት ሁኔታ መኖሩን እያወቁ የወደፊቱን ራዕይ ከዛሬዉ እዉነታ ጋር አጣፍጦ መተግበር ተስኗቸዉ ሰለ ልዩነት ሰለ መገነጣጠልና ክህደት ስለ ግለኝነትና ራስ ወዳድነት መታገልና መወያየትን ከሁሉ በላይ ቅድሚያ ሰተዉት ሲነሱ ሲወድቁ ኖሩበት አሁንም ሙጭጭ ብለዉበታል

ልብ በሉ የሚገርመዉ እና ትንሽ እንኳን እፍረት የማይሰማቸዉ ብሄረሰባዊ ድርጅት ተብየወች ህዝቦች ቋንቋ ሀይማኖት ባህል ባጠቃላይ ብሄረሰባዊ ክልል ሳይወስናቸዉ ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ተሰልፈዉ በመዉጣት ኢትዮድያዊነትን ማስቀደማቸዉን እያዩ በምርጮ 97 የታየና የተገኘዉን ህዝባዊ ድል እና የህዝብ ድምፅ እየተገነዘቡ የባድመን ድል እያስታዉሱ በወፍ ዘራሹ የወያኔ ጥይት በየጎዳናዉ የተሰዉት ዜጎች ተንተርሰዉ የወደቁበት የወያኔን ዉልደት የክልል ጨርቅ ሳይሆን የአልፋና ኦሜጋ ዉጤት ባአያት ቅድመአያት በህዝቦች ደምና አጥንት ባሸበረቀዉ እና የህዝብ ፍቅር በሆነዉ በኢትዮጵያ ብሄራዊ ሰንደቃላማ ላይ መሆኑን አይናቸዉ እያየ ለህዝብ ፍላጎት መገዛት አልያም ድርጅታቸዉን ማጥፋት አለመቻላቸዉ ነዉ

ሌላዉ የተሻለና መልካም ራእይ ይዞ የሚነሳ ብሄራዊ ድርጅት እንኳን ቢኖር ገና በእንጭጩ እንዳለ በተለመደዉ የኗልዮሽ ጉተታ አንድ እርምጃ ሳይራመድ ከቀለበቱ ገቡቶ ራሱም የዚያዉ የኗሊዮሽ ጉዞ ተባባሪ መሆኑ ነዉ ኢህአፓ መኢሶንን ጣለ መኢሶን ኢህአፓን ጣለ ኢፒዲኤ ኢድህን ጣለ ኢስፓአኮ ኢማሌድሕን ዉጦ ደርግ 17 አመት ረግጦ ገዛ ከደርግ መዉደቅ በኋላ ያዉ በሽታ በሌሎችም የፖለቲካ ዱርጅቶች እንደ ዉርዴ በመተላለፉ ኢደፓ ቅንጅትን ግንቦት 7 ቅንጅትን አንድነት ቅንጅትን መኢአድ ቅንጅትን ኢህአፓ ኢህአፓን ሌላም ሌላዉን ሲጥል ወፍ ዘራሹ ዉያኔ በጥይት መግዛቱን ተያይዞታል

በፖለቲካ ድርጅቶች መካከል ልዩነት መኖሩ የህልዉናቸ መግለጫ ቢሆንም የመጠፋፋቱ አባዜ የፖለቲ ልዩነት ሳይሆን የራስ ወዳድነትና የኔ ብቻ ባይነት በሽታ ነዉ በዚህ መርዝ አንድ ትዉልድ ወድሟል የዚህ ትውልድ ኢኮኖሚም ተመሳሳይ እጣ ገጥሞታል አንዳንዴ የኗላውን መለስ ብየ ሳስታዉሰዉ ዛሬ ብሄራዊ እርቅ የምንለዉን በሰከነ መንፈስ የሀይለስላሴ መንግስት አግኝቶት ቢሆን ኖሮ አገር ባልተበጣጠሰ ትዉልድ እና ኢኮኖሚዉ ባልወደመ የዲሞክራሲ አቋራጭ መፍትሄዉም ላመታት ባልተለጠጠ ነበር እልና የደርግን ሆነ የወያኔን መንግስት ለዉጥ ብኩን ሂደት እለዋለሁ

ህዝብ የተጠየቀዉን ሁሉ ሆኗል ለአንድነት ለአገር ሉአላዊነትና ለዲሞክራሲያዊ መንግስት ስርአት ግንባታ አሁንም ያሉትን ሆኖ ለመገኘት ምን ጊዜም ዝግጁ ሆኖ ይታያል እንወክልሀለን የሚሉት ፖለቲካ ድርጅቶች ግን ራስወዳድነት አላማ ቢስነት እቅጣጫቸዉን እያሳተ ከህዝብ ፍላጎትና የአላማ ድናት ጋር አብረዉ ካለመኝዝ አልፈዉ ለቅራኔወች ሰላማዊ መፍትሄ ባለመሻትና የልምድና የአመራር ብቃታቸዉ ማነስ ህዝብ በንብረቱ በእዉቀቱና በደሙ የገነባዉን ድርጅት ሲንዱትና እንዳሻቸዉ ሲበጣጥሱት ይታያል የሚገርመዉ አብዛኛወቹ ፖለቲካ ድርጅቶች በህዝብ ወይም በአባላቱ ዉሳኔ የሚገዙ ሳይሆን እንደ ግለሰብ የግል ንብረት እቃ የሚከናወኑ ናቸዉ

በተለይ ኢህአፓና ቅንጅት ይህም ከነበራቸዉ ህዝባዊ ድጋፍና ድርጅታዊ ጥንካሪ አኳያ ሲታይ ማእከላዊ አሰራሩ ማለት ታህታይ መዋቅሩ ለላእላይ መዋቅሩ አመራርና ዉሳኔ ተገዥነቱን ሲያሳይ ላእላይ መዋቅሩ ግን ለታህታይ መዋቅሩ ድምጽና ዉሳኔ ተገዥ ሆነዉ አያዉቁም ቢያንስ ቢያንስ የተከፈለዉን መስዋአትና የህዝቡን ታሪክ ሰሪነት ግምት ዉስጥ በማስገባት ከነሱ መገነጣጠልና የመጠፍፍት ታሪክ በፊት የህዝቡ ፍላጎት የአባላቶቻቸዉ አስተያየት የወያኔ ሂወትና የወቅቱ ፖለቲካ ተጨባጭ ሁኔታ መገምገም ነበረበት

ለነገሩ ህዝብና አባላቶቻቸዉ ለነሱ የጋሪ ፈረስ ናቸዉ በየዉስጣቸዉ መጠነኛ ለዉጥ ቢኖርም ለችግሮች ሳይንሳዊ መፍትሄ ተፈልጎ በረቀቀ ድርጅታዊ ስራ አንድነቱና የአባላቱ ጥንካሬ ሳይናድ ለዉጥን ማምጣት ሲቻል መፍትሄ ሆኖ ያገኙት ከሁለትና ሶስት መቆራረጥ ሆኖ የአንድነት ሀያልነትን በመዘንጋት የጋራ ጠላትና አላማዉ ተረስቶ ትግሉ በነሱ ዙሪያ ሆነ የታገሉለትን አላማም መልሰዉ ጦርነት ሲገጥሙትና ሲወነጅሉትም አየን ይህደግሞ ስልጣን በተፈለገዉ አይነት መንገድ ይምጣ ወደሚለዉ የሽክርክሪት ታሪካችን የሚመልሰን ነዉ በጥሩና አተማማኝ መሰረት ላይ ያልተገነባ ስራ ዘለቄታ እንደማይኖረዉ እየታወቀ ያንኑ በመደጋገም ያላንዳች አስተማማኝ ለዉጥ እዚህ ደረስን ሌላዉ የሚገርመዉ በፖለቲካ ድርጅቶች ድክመት የልማት የእድርና የተለያዩ የሰንበቴ ማህበራት ለአገርና ህዝብ ያላቸዉ ቅን አመለካከት የሚያስመሰግን ቢሆንም የወከሉት ስራ ተዘንግቶ የፖለቲካ ስራዉን በመረከብ ባለህበት ዙር እያሉን ነዉ እንደ ፖለቲከኞች አባባል አገር መዉደድና ፖለቲከኛ መሆን ይለያያል ማህበራት ፖለቲከኞች ባለመሆናቸዉ ፖለቲካዉን ነፍስ መዝራት ስለማይችሉ ሁሉም በየፊናዉ በሚያወጡት ፖለቲካዊ መግለጫ የፍጌል ወጠጤ ፉከራ እያሰሙን ነዉ የትኛዉ ፖለቲካ ድርጅት የትኛዉ ማህበር እንደሆን ለመለየት እያስቸገረ ነዉ ይህ ሁሉ ጠንካራና ህዝባዊ መሰረት ያለዉ አስተማማኝ ድርጅት ያለመኖር ያስከተለዉ የግብር ይዉጣ ስራ ዉጤት ነዉ

ስለአገር አንድነት ስለህዝባዊ መንግስት ምስረታ በታሪክ በአገር ቅሪት ላይ ሁሉም ተቃዋሚ ድርጅቶች ተመሳሳይ አቃም እንዳላቸዉ በቀን ተቀን የፕሮፖጋንዳ ስራቸዉ ሲያስረዱን ኖረዋል ይህ አቋማቸዉም በወያኔ ኢህአዴግ ላይ ያላቸዉን ተመሣሣይ እምነት ያስረዳል

እንግዲህ ኢትዮጵያ በምንም አይነት መልኩ ያንድ የፖለቲካ ቡድን ወይም ድርጅት ብቸኛ አገር ልትሆን አትችልም የቡዙ ችግሮች ባለቤቶች ነንና እንደየ ችግሮቹ የተደራጁትን በማክበር በጠበቀ መቻቻል ላይ የተመሰረተ አንድነት የፖለቲካ ራእይ ይዘዉ የተነሱ ብቻ በአሸናፊነት እንዲወጡ ማዱረግ የዘለቄታ ችግርን የሚፈታ ይመስለኛል

በዚህ በኩል እንጋፋዉና የእድሜ ባለጸጋዉ ኢህአፖ ለበሽታዉ መድሀኒት ሊፈልግ ይገባል እነሱ ከያዙት የተሻለ ነገር መፍጠር ያላደጉበት ነዉና አይዋጥላቸዉም እነሱ ያልመሩት የፖለቲካ ትግል እርባና የለዉም ልዩነትን በሰላማዊና በሰለጠነ መንገድ ማስተናገድ ተስኗቸዉ አዲስ ነገር መፍጠር ባለመቻላቸዉ ዝንተአለም ዳዴ ሲሉታሪክና እድገታቸዉ በወረቀት በዘፈን በቀረርቶና በለቅሶ ብቻ ታግቶ በነበረ መኩራራት ብቻ ሆነ ትርፉ ያልሰለጠነ ዉጤታቸዉም ያስከተለዉ ዉጤት መፈረካከስ ሆነ

የህብረት እና የአንድነት ጥያቄ ጎልቶ በታየበት አለም ልዩነትን አቻችሎ ቅድሚያ ሊሰጠዉ በሚገባ ጉዳይ ላይ ማተኮር ሲገባ ቡድን ለይቶ አንዱ አንዱን ሲያወግዝና የድርጅቱን ዉስጠ ህይወት አደጋ ላይ ሲጥሉት አየን ኢህአፖ በጣፈጠ ቋንቋና አቀራረብ ያልተሟገታቸዉ ድርጅቶች ሆኑ እዉቅ ግለሰቦች የሉም ፕሮፌሰረ አስራትን በየመድረኩ ሲገዘግዙ ቆይተዉ ከሞቱ በኋላ የመጀመሪያዉ አልቃሽ

በመሆን ፎቶግራፋቸዉን በአበባና በባንዴራ ያሸበረቁትን ማስታወስ ይቻላል የቅንጅት መሪወች በግንቦቱ ምርጫ ለመሳተፍ ደፋ ቀና ሲሉ የምን ተሳትፎ ነዉ እያሉ ሲያንቋሽሹ ሰንብተዉ ቅንጅት በርካታ ወንበር አገኘ ሲባል አድናቆታቸዉ ገለጹ ታሰሩ ሲባል በየአደባባዩ ለመታየት ሞከሩ ታሰሩ ሲባል አንድነታቸዉ እንዲቦረቦር የከሌ ቡድን የከሌ ቡድን እያሉ በየከተማዉ ባሉ ካድሪወቻቸዉ ከወያኔ ባላነሰ የብተናና የስም ማጥፋት ዘመቻቸዉን ቀጠሉ

ለቅንጅት መከፋፈል ቅድሚያ ተጠያቂዉ የቅንጅት አመራር አካላት መሆናቸዉ ታሪክ የማይረሳዉ ጠባሳ ሂወታቸዉ መሆኑን ብንረዳም ዉርዴዉ ተያይዞ የመጣ ነዉ ቅንጅትም ሆነ ኢህአፖ ተከፋፍሎ አንዱ ከሌላዉ የሚሻል መሆኑን ለማረጋገጥ የሚደረገዉ ትግል ከዋናዉ የትግል አቅጣጫ መስመር ወጥቶ ወዲያና ወዲህ እየተናጉ ያንዱ ቁስል ሳይደርቅ አንዱ እየቆሰለ የቀድሞዉ ቁስል ተመልሶ እያመረቀዘ የፖቲካ ዉርዴዉ ቡዙወችን እየገደለ ይገኛል ትግሉ በየአቅጣጫዉ ተፋፉሞና ከአገር ዉስጥ አልፎ የሞላዉን አለም ህዝብ ትኩረት በሳበበት ወቅት የዘመናት ተጋድሎ ዉጤት የሆነዉ ድርጅታቸዉን ካደጋና ከመከፋፈል ማዳን ያልቻሉ ኢትዮድያን የምታክል የተወሳሰበና የቡዙ ታሪክ ባለቤት የሆነች አገር ተረክበዉ ለመምራት ስለመቻላቸዉ ጥያቄ ዉስጥ እየገባሁ ነዉ

በስልጣን ላይ ያለዉን መንግስት ሀገርና ህዝብን በመግደል ስንኮንነዉ ለሀገር ተስፋ የሚሆኑና ይሆኑ የነበሩ መሪወችን ሞራልና ስሜት ባሉባልታና ሀሜት በተራ ስም ማጥፋት ከትግ እንዲገለሉ ያደረጉ የመንፈስ ገዳይ ቡድኖችና ግለሰቦችም ከህሊና ቁስል ነጻ አይደሉም የሚገርመዉ ከፖለቲካ ኀጠኝነት በጸዳ ኢትዮድያዊነትን ቅድሚያ ሰተዉ ተጨባጩን የአገር ሁኔታ በመሞርኮዝ የአገር ሉአላዊነትን ለማስከበር የሚያስቡና የሚደክሙ ሂወታቸዉን ከአገርና ከወገኖቻቸዉ ደህንነትና መብት ጋር አጣምረዉ የሚያዩ ወገን ሲቸገርና አገር ሲደፈር በዝምታ ማለፍ የማያስችላቸዉ ሰወች እንኳን የዉግዘቱ ሰለባ ሆነዋል እንዲ አይነቱን የዉግዘት ጽሁፍ ለጊዜያዊ ፖለቲካ ፍጆታ ሊጠቅም በሚችል አይነት መልኩ የስንጠቃ ዉርጅብኝ ማዥጎድጎድ በተቻለ ነበር ቁምነገሩ የምንኮንነዉን ሆነን ስንገኝ በህዝብ ሆነ በራስ ህሊና ተጠያቂ መሆኑ የማይቀር በመሆኑ ጉዳዩን ለጊዜና ትዉልድ ሰጥቸ አልፈዋለሁ

ትላንት ኢትዮጵያ እንደሌሎች አገሮች አድጋ እንድትታይ በመፈለግ በንጹህ የአገር ፍቅር ስሜት ብቻ በስሩ የተሰባሰቡ ምርጥ የአገሪቱ ዜጎች በተሳሰተ አመራር በደርግና በራሳቸዉ ጥይት አካላቸዉ እንዲጎድል ንብረታቸዉ እንዲጠፋ ሂወታቸዉ እንዲያልፍ አድርገዉ

ትላንት ለአገር ሉአላዊነት መከበር ከሶማሊያ ወራሪ ሀይል ጋር ደሙን ሲያፈስ የነበረዉን ሰራዊት ምራል ለመስበር የተወሰደዉን የፖለቲካ ቁማር በመዘንጋት የሀገር ክህደትን ለመሸፈን ሞከረዉ

ትላንት የኤርትራን መገንጠል በግንባር ቀደምትነት ሲደግፉ ቆይተዉና በብሄር ብሄረሰብ ጭቆና ስም የተሳሳተ የፖለቲካ መርዝ ረጭተዉ የአገር ሉአላዊነትና ህዝብን ማድማታቸዉ አልበቃ ብሎ

እድሜ እየገፋ ሲሄድ አእምሮም በይበልጥ እየዳበረ ችሎታም በዚያዉመጠን እንደሚበለጽግ ከታሪክ ምስክርነት ባለመማር ከሁለት ተከፈሉ

ብቻ አንቱ የተባሉ ለአገርና ህዝብ ጠበቃ የሆኑ ሀይሎችንና ቡድኖችን ተከታትሎ ማጥፋትና አጥንትን የሚሰብር የስድብ ዉርጅብኝ ማዥጎድጎድ ስራየ ብለዉ ተያይዘዉታል

ለዚች አገር መሪና ህዝባዊ መሰረት ያለዉ ድርጅት አሳጡን አገርና ህዝብን ያድናሉ ይመሩናል የሚል እምነት የጣልንባቸዉ አንዳንድ ምሁራንም በሚወረወርባቸዉ ዱላ ሳቢያ ዝምታና አርቆ ተመልካችነትን መረጡ ዲሞክራሲ ያለመስዋእት ይገኝ ይመስል ችግርን ፊትለፊት የመጋፈጥ ባህሪ አጡ ቀናና ቀጣዩን መንገድ መሻት ተዘንግቶ ታሪክ ሰርተዉ ላለፉት ማልቀስና ወይኔ ነዶ ማለትን ስራየ ብለዉ ተያያዙት ለአገርና ህዝብ ቀና ህይወት የነበራቸዉ አብዛኛዉ የኢህአፖ አባላት ግን የከፈሉት ለዚህ አልነበረም ኢህአፖም ሆነ ጥቂት አባላቶቹ ከዚህ አዙሪት የምትላቀቁበት መፍትሄ ቢፈለግ የተሻለ ነዉ ድክመት ወይም መሸነፍ የሚለዉ ቃል ቶክክለኛ ትርጉሙ መዉደቅ ሳይሆን ወድቆ መቅረት ነዉ እንደተባለዉ ሁሉ ከተጠቀማችሁበት ጊዜና ህዝብ አለ

የደም ንግድ ግን ይቁም በብሄር እና ብሄረሰባዊ ድርጅቶች

ሰላማዊ ትግሉ ዲሞክራሲን ከማስፈን በላቀ ለአገር ህልዉናም አስተማማኝ በመሆኑ ያለፈዉ ትግል ካሁኑ ተጨባጭ ሁኔታ አስተምሮን ያለፈ ተሞክር ቢኖር መገነጣጠልና የኔነትን ብቻ በመሆኑ ካለምነዉ ግብ መድረስ ተስኖናል በተበጣጠሰና ሕዝባዊ ሀይል በሌለዉ ድርጅት ይችን አገር ዲሞክራሲያዊ አመራር ማስጨበጥ የማይቻል በመሆኑ በብሄር ሆነ በብሄረሰብ ስም የተደራጁ ድርጅቶች ሁሉ ደንባቸዉን በመመርመር የተጠናከረ ህብረት መፍጠር ይገባቸዋል አንዱ አንዱን እየወነጀለና ዲሞክራሲን ትርጉም እያሳጡ ስለህዝባዊ መንግስት መጮህና ወያኔን ለድርድር መጋበዝ የህልም ስልጣን መያዝ ይሆናል የእስከአሁኑ ተሞክሮ ያስገኘዉ ዉጤት አለመኖሩን በመገንዘብ በየትኛዉም መንገድ የተሰባሰበ ይሁን ህዝባዊ መሰረት ያላቸዉና ከቡድናዊ ስሜት የጸዱ ሀይሎች ተሰባስበዉ በአንድ ጊዜያዊ ደንብ በመመራት በመንግስትና በፖለቲካ ድርጅቶች እዉቅናን ካገኙ በኋላ ለሁሉም ጥሪ በማስተላለፍ ጉዳዩ በሰላማዊና ብሄራዊ እርቅ መፍትሄ የሚያገኝበትን መድረክ ማመቻቸት ለህዝባዊ መንግስት ምስረታ ጥሪ ተገዥ የማይሆኑትን ድርጅት ሆነ መንግስት ህዝባዊ መሰረት ማሣጣት የእለት ተእለት ተግባራቸዉን ማጋለጥ መንግስት ለዘላቂ መፍትሄው በጎ ምላሽ ምቹ ሆኖ ካልተገኘ ድርጅቶችን በማስተባበር እና አንድ በማድረግ ወቅቱ በፈቀደዉና አማራጭ ሆኖ በተገኘዉ መንገድ መንግስትን መፋለም የሚቻልበትን ሁኔታ የሚያመቻች ሀይል ሊፈጠር ቢችል ያገር ችግር አቋራጭ መፍትሄ ባገኘ ነበር እላለሁ

እርግጠኛ ነኝ ጥቃቅን የአፈጻጸም ልዩነቶች ለጊዜዉ ደንቃራ ቢሆኑም በአብዛኛዉ ላገር ሉአላዊነትና ለህዝብ ዲሞክራሲ የተሰለፋችሁ በመሆኑ ለጊዜዉ መስሎአቹህ ላለመግባባት ተማምላችህ ብትደራጁም የኋላ የኋላ በህዝብ ተጽኖ የምታከናዉኑአቸዉ ተግባሮች ለማህላችሁ መፍረስ ምክንያት ሆኖ ሊያሰባስባችሁ እና አንድ ሊያደርጋችሁ እንደሚችል ጽኑ እምነት አለኝ

በመጨረሻም
======================

በነበረዉ ሆነ በአሁኑ ምስቅልቅል የፖለቲካ ችግራችሁ የምትጓዙ ከሆነ ግን
ህዝቡን ገንዘብ አዋጣ ተሰለፍ ታሰር ሙት ተሰደድ ጸሎት አድርግ ሻማ አብራ
የስራ ማቆም አድማ አድርግ ከማለት አልፋችሁ ለስልጣን አትበቁም ህዝብንም
የስልጣን ባለቤት ማድረግ አትችሉም

የደም ንግድ ነጻ ወቶ አይቸዉ
ሁሉን ማድረግ የማይሳነዉ አምላክ ልቦና ይስጣችሁ

ከካሊፎርኒያ ሳክራሜንቶ

www.ethiomedia.com – a site of alternative news and views